# ወያኔዎች የደርግ ስጦታዎች ናቸው ፤
# መንግሥቱ ሃ/ማ ባነጠፈላቸው አዳራሽ ነው የጨፈሩት

ታጠቅ መንጂ

አገስት **21/2018**

መንግሥቱ አንጋሾች ማለት የመንግሥቱ ሹማምንቶችና ካድሬዎቹ ስለመንግሥቱ ሃ/ማ ሃሳብ በተሰነዘር ቁጥር 'መንግሥቱ አገሩን ይወዳል' ማለት ይቀናቸዋል፤በዚህ አባባላቸው በጣም እናደዳለሁ ። የአንድ አገር መሪ የሚመራውን አገር የመውደድ ትርጉም ምንድነው? በምንስ ይለካል? የዚያን ሉዓላዊ አገር ምድሩን ብቻ መውደድ ማለት ነውን? የሚመራውን አገር ሕዝብ ፀር መሆን ነውን? የዚያን አገር የተማረውና ያንን አገር አልሚ ምሁራንን መጥላትና መጨፍጨፍ ማለት ነውን? የዚያን አገር ዳር ድንበር የሚያስከብሩ መኮነኖችን በጥይት መመንጠር ማለት ነውን? ጦር ሜዳ ላይ የተሰለፉ መኮንኖች ቁጥ በሳንጃ መውጋትና መፎከር ማለት ነውን? የሚመራውን አገር ሕዝብ ድሃ በመሆኑ "የዚህን ዓይነት ድሃ አገር ፕሬዝዳንት ከመሆን ………… ይሻላል" በማለት የሚያስተዳድረውን አገርና ሕዝብ መናቅና ማንቋሸሽ ማለት ነውን ? የሚመራውን ሕዝብና አገር አደጋ ላይ ጥሎ ቤተሰቡን ሰብስቦ መሸሽ ማለት ነውን?

በሌላ አነጋገር ከዜጎች በፊት አገር ማስቀደም፦ ከፈረሱ ጋሪውን ማስቀደም ፣ከተማሪዎች ደህንነት ትምህርት ቤቱን ማስቀደም፣ከወታደሩ ጠመንጃውን ማስቀደም፣ከእረኛው ከብቶችን ማስቀደም ወዘተርፈ አይሆንምን? የሚመራውን ቤተክርስቲያን ምዕምናን ገሎ የጨረሰ ጳጳስ ወይም ቄስ ሃይማኖቱና ቤተክርስቲያኑ ይወዳል ማለት ይቻላልን?ተዋጊ ሠራዊቱን ያስጨረሰ መኮነን ጎበዝ አዋጊ ሊባል ነውን? እያለው ልጆቹን ያስራበ አባት ልጆቹን ይወዳል ማለት ይቻላልን? በጎችን ለአውሬ ያስበላ ወይም ያስራበ እረኛ ትጉህ እረኛ ነው ማለት ይቻላልን?

መሬት ወይም አገር የዜጎች ንብረት ወይም ይዞታ እንጂ ዜጎች የአገሩ ወይም የመሬቱ ንብረት ወይም ይዞታ አይደሉም (**the land of a country or a country itself is object to subjects or citizens not vise versa).**አገር ያለ ሕዝብ የውሬዎች መፈንጫ ነው። ሃሳባዊ/ስሜታዊ አባባል እና ጭብጣዊ ሁኔታዎች እየብቻ ናቸው፤ነገሮችን ሰንጥቀንና ፈታትን ማየት ያስፈልጋል። በርግጥ፦ሂትለርም፣ ሞሰለኒም፣ የስፔኑ ጀነራል ፍራንኮም ፣የኢንዶዥያውም ሰኋርቶ፣ችሊያዊውም ፒኔቾም ፣ረሺያዊውም እስታሊን፣ዩጋንዳዊውም ኢዲያሚን፣ካቦዲያዊውም ፖልፖት ወዘተ..ደጋፊዮችና አሚካሾች ነበሯቸው ፤ውሻ በበላበት ይጮሃልና ።

የአገር ወዳድ መሪ ሚና በግርድፉና በቁንጽሉ

ሁላችንም እንድምናውቀው ሥልጣን ሃይል ነው ፣ ለጥሩም ለመጥፎም ሥልጣን ሌሎችን ካልተቆጣጠረና ለራሱ ነጻነት ካልሰጠ ሥልጣን ትርጉም የለውም ። የአንድ ሉዓላዊ አገር መሪ በምንም ዓይነት መንገድ ሥልጣን ጨብጦ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት እውቅና ከሰጠው ፤ ያ መሪ ራሱ የዚያ አገር ሉዓላዊ ነው ። የዚያን አገርና ሕዝብ ሉዓላዊነት፣የዚያን አገር የምጣኔ ሃብት ፣ የዚያን አገር መከላኬያ ሃይል ፣ ፖሊስ ሰራዊት፣ ተቋማት ወዘተርፈ በመሪዩ ሉዓላዊነት ሥር ነው የሚውሉት ። በሌላ አነጋገር የመሪዩ መንግሥት የሥልጣን ምንጮች ናቸው ፤በተለይም የሚያስተዳድረውን ወይም የሚመራውን ሕዝብ።

አንድ አገሩን የሚወድ ብልህ መሪ -የሥልጣኑ ሁሉ ቁንጮ ወይም እምብርት ዜጎቹ መሆናችው ጠንቅቆ ያውቃል፣ ዜጎቹን ይወዳል፣ያከብራል፣ዜጎቹን ያማከለ/ፒፐል ሴንተረድ አስተዳደር ይከተላል። አገሩን የሚወድ መሪ ለፖለቲካ ሥልጣን ሲመኝ -ከላይ ከዚህ አንቀጽ ከፍ ብሎ የጠቀስኳቸውን የሥልጣን ምንጮች ተጠቅሞ የሚመራውን ሕዝብና አገረ በቅንነት ለማገልገል ነው ።

በራሱ ሕዝብ ይተማመናል፣ ዜጎቹ በሕግ ፊት እኩል መሆናቸውና ማኅበራዊ ፍትኅ መኖሩን ያረጋግጣል ፣ለታሪኩ፣ለባህሉና ለቋንቋው ቀናኢ ነው ፣ የሚፋቀርና አገሩን የሚወድ ሕዝብ እንዲኖረው ይጥራል፣ ገዢያቸው ሳይሆን አገልጋያቸው እንደሆነ በተግባር ያሳያል፣ዜጎቹን ከመሰረታዊ ፍላጎቶች (ከምግብ፣ከጤና፣ ከትምህርት ፣ከንጹህ ውሃ፣ከመኖርያ ቤት፣ከመጸዳጃ ወዘተርፍ እጦቶች/ችግሮች)ለማላቀቅ ይጥራል ። የተከበረ ሕዝብና የማይደፈር አገር ለማቆየት የሚያስችሉ አገር በቀልና ባዕድ በቀል የጭንቅላትና የቁሳቁስ ምንጮች ሁሉ ይጠቀማል ።አገሩ በኢንድስትሪ፣በተክኖሎጂ፣በኮሚኒኬሽን ፣ በግብርና፣ በኪነጥበብ፣ በመከላከያ ፣ በትምህርት፣በሳይንስ ፣ በንግድ ፣በመንገድ ዝርጋታ ወዘተርፈ ለማሳደግ፣ ለማልማትና ለመገንባት ይኳትናል ። የአገር መውደድ ትርጉም እንካንስ ጀሌዎቹ መንግሥቱም አያውቀውም።አጼ ምኒሊክ ሕዝባቸውን በመውደዳቸው ፣ለሕዝባቸው ላቅ ያለ አክብሮት ስለነበራቸውና በሕዝባቸውም በመውደዳቸው ነው የአደዋን ድል የተቀዳጁት። መንግሥቱ ሃ/ማርያም ግን ፀረ-ሕዝብ በመሆኑ አውዳደቁን ዓይተናል።

መ/ሃማርያም ወያኔዎች እንዴት ኢትዮጵያን እንዲገዙ መንገዱን እንዳመቻቸላቸው ፤ እንዴት ባነጠፈላቸው አዳራሽ ለመጨፈር እንደበቁ ፦

1.በግምት ከ 300,000 በላይ-እጅግ በጣም የሰከነ/የመጠቀ ማኅበራዊና ፖሊቲካዊ ንቃተ-ኅሊና የነበራቸው፣ በሕዝባቸውና በሀገራቸው ፍቅር የታነጹ ፣ፍጹም ጀግናና የኢትዮጵያ አለኝታ የነበሩ ወጣት ፣ኅልማሳና አዛውንት ምሁራንን በጥይት አስመተረ፣አስከሬናቸውን ሸጠ፣በሬሳቸው ነገደ፣ከእነዚህ ውስጥ የ 13 እና የ 14 ዕድሜ

ሕጻናት ይገኙበታል፣ስድስት <6> ወጣት ልጆቻቸውን የተገደሉባቸው ወላጆች ነበሩ፤ አሁን በሕይወት አይኖሩም፣ ወላጅና ቤተሰብ እንዳያለቅስላቸው ከለከለ/አሳገደ።

ብዙ ሺዎች በሰቆቃ ሕይወታቸው አጡ፣ብዙ ሺዎች በሰቆቃ አካለ ጎደሎ ሆኑ፣ብዙ ሺዎች በሰቆቃ የአእምሮ በሽተኛ ሆኑ፣ብዙ ሺዎች በሰቆቃ የተባዕታይ እና የዕንስታይ ብልቶቻቸውን ተኮላሽቶ ፍሬ/ዘርአልባ ሆኗል ወዘተርፈ። ለምን? ምን ስላደረጉ?

የኢትጵያ ሕዝብ (ፖለቲካዊ፣ስባአዊ፣ሲቪላዊ እና ሃይማኖታዊ) መብቶች ይከበሩ!

ነጻ የፖለቲካ መድረክ (የመሰብሰብ፣የመጻፍ፣የመወያየት፣የመደራጀት ወዘተ..)ነጻነት ይኑረን!

በዲሞክራሲያዊ መተክልና አሰራር ሕዝባዊ መንግሥት ይመሥረት!

ዜጎችን በእኩልነት የሚዳኝ የፍትህ ሥርዓት ይኑረን! የሕግ የበላይነት ይከበር!

ዜጎች መሰረታዊ የሕይወት ግልጋሎት (ምግብ፣ ውሃ፣ መጠሌያ ፣ህክምና፣ትምህርት፣መጸዳጃ ወዘተ..) ያግኙ ።በርንዳ አዳሪነት፣ረሃብ ፣ጉስቁልናና ልመና ያብቃ!

እህቶቻችንንና እናቶቻችን በጾታቸው የሚድርስባቸው ጭቆና ያብቃ! ይወገድ! መሬት ላርሶ አደሩ ይሰጥ! የጭቁን ወታደሮችና የጭቁን ሠራትኞችን የነፍስ ወከፍ ገቢ ይሻሻል! ጭቆናና ብዝበዛ ይወገድ! በማለት በስላማዊ መንገድ ሰልፍ ስለወጡ፣አቤቱታ ስላቀረቡ፣ ስለተማጸኑና ስለጮሁ ብቻ ።

2. በካድሬዎቹ አቃጣሪነት - ከብዙ ዓመታት የአካዳሚክ ትምህርት፣ የውትድርና ብቃትና ልፋት በኋላ ያገኙትን ማዕረግ ወደ ተሰማሩበት ጦር ሜዳ ድረስ በመሄድ ፣ በሚያዙትን ሠራዊት ፊት - ከትከሻቸው ላይ በመቀስ ቆረጠ ፣በጥፊ መታቸው፣ቂጣቸውን በሳንጃ በመውጋት ከአዋርዶና ቅስማቸውን ከሰበረ በኋላ እዚያው በሰራዊቱ ፊት አስረሸናቸው ። ቂጣቸውን በሳንጃ እየወጋሁ! ማዕረጋቸውን እየቆረጥኩ!በጥፊ እየመታሁ! ወዘተርፈ ብሎ ተኩራራ፣ፎከረ፣አቅራራ። ይህ ከአንድ መሪ የሚጠበቅ ባህሪ ወይስ በጠመንጃ አፈሙዝ ቤተመንግሥት የተቀመጠ የጎዳና ዱርዬ፣የጎዳና ተደባዳቢ፣የጎዳና ወሮበላ/gang ባህሪ?

3.ጀነራሎች፣ኮለኔሎች፣ሻለቆችና ሻምበሎች በተራ ወታደራዊ ካድሬዎች እንዲታዘዙ፣በጥፊ እንዲመቱ ፈቀደ፤ ከወታደራዊ እዝ የሚመጡትን ትእዛዞችን ማስቀየር የሚያስችል ሥልጣን ሰጣቸው። መኮነኖች ለማን/በማን እንደሚታዘዙ ማወቅ ተሳናቸው፤ግራተጋቡ

4.ከደርግ ሹማምንቶችና ከሠራዊቱ ለሻቢያና ለህወሃት የሚሰልሉና ሚስጥር የሚያቀብሉ እንደነበሩም ተወርቷል፣ ይወራል

5.የወታደራዊ ካድሬዎች ሚና የመንግሥቱን ሥልጣን መንከባከብ ስለነበረ፣በሠራዊቱ መካከል መተማመን አልነበረም። ሞያዊም ሆነ ግላዊ ብሶታቸውን እንዳይተነፍሱ ፍርሃት አሰፈነውባቸው ስለነበረ ፣በርካታዎች ለአእምሮ በሽታ ተዳረጉ፣በብዙ ሺዮች የሚቆጠሩ እጃቸውን ለወያኔና ለሻቢያ ሰጡ፣ሆን ብለው ምርኮኛ ሆኑ "በፖለቲካ ዕዝ ሥር ወድቆ በአስተዳደራዊ ትብታብ ታስሮ በወታደራዊ ስትራተጂና ታክቲክ ድክመት እንዲሁም በሎጂስቲክ አቅርቦት እጥረት ተሽመድምዶ ለተሸነፈው የኮሩ ሠራዊት…ውድቀቱ አሳዛኝ ፍጻሜ ሆነ። በ 1979 ዓ.ም መጨረሻ ላይ የተመሠረተውና 604 ኛ ኮር ተብሎ የሚታወቀው ሠራዊት፡-ትኩረት ተነፍጎት 'በጦሩ አዛዦች ሳይሆን በፖለቲካ መሪዎች አመራር ሥር ወድቆ' ለሽንፈት የተዳረገ ጦር ነበር" (ሻለቃ ንጋቱ ቦጋለ፣የመጀመሪ ዕትም 2004፣ገጽ 14)።

6.እ.ኢ.አ በ 1981(እ.አ.አ በ 1989)ዓ.ም በመንግሥቱ ሃ/ማ ላይ መፈንቅለ መንግሥት ታቅዶ እንደነበረ ያኔ በሕይወት የነበርን አሁንም በሕይወት ያለን ኢትየጵያውያን ሁሉ የምናውቀው ነው።መፈንቅለ መንግሥቱ የከሸፈው አንድ ከአመሪካ የስለላ ድርጅት <C.I.A> ጋር በሚሰራ የቀድሞ የደርግ መኮነን ለመንግሥቱ ሃ/ማ የፕሮቶኮል ጸሃፊ <ለመንግሥቱ ገመቹ> ባደረገው ጥቆማ መሆኑን በተለያዩ ኢትዮጵያውያን ተደጋግም ተጽፎ አንብበናል። በዚያ ምክንያት 26 ከ 25-30 ዓመት ለአገራችን ለኢትዮጵያ ወታደራዊ አገልግሎት የሰጡ ጀነራሎች እና 4 እስከ ኮሌኔልነት ማዕረግ የነበራቸው መኮነኖች ያለፍርድ በጥይት ተደመሰሱ ። ከእነዚህ ውስጥ 12 ቱ በአገልግሎት የሚበልጡ/ሲኒየር ጀነራሎች በአዲስ አበባ በወታደራዊ ፍርድ ቤት/ኮርት ማርሻል ትእዛዝ ተረሽነው በአንድ ጉድጓድ ተቀበሩ ።

14 ቱ ጀነራሎችና 4 ቱ ባለ ልዩ ልዩ ማዕረጎች በአስመራ በደርግ ካድሬዎች ዘግናኝ ሰቆቃ ከተፈጸባቸው ወይም ቶርች ካደርግዋቸውና በጥይት ደብድበው ከገደሏቸው በኋላ የከፊሎችን አስክሬን ከጂፕ መኪናዎች ኋላ በአህያ መጫኛ ገመድ አሥረው በአስመራ መናኸርያ ጎዳናዎችና መንገዶች እየጎተቱ ለከተማው ሕዝብ እንደ ትዕይንት አሳዩ ፣እንደ ትዕይንት ታዩ ። አስከሬናቸው በመጫኛ ከተጎተቱት አንዱ የአስመራ ክ/ጦር አዛዥ የነበሩት 'ጀነራል ቡልቱ ደምሰው' ናቸው (ዘነበ ፈለቀ፣ነበር መጽሃፍ፣2001፣ቅጽ 2፣ ገጽ 256)። የ 18 ቱም ሬሳ በአንድ ኮረፐታ ሥር ተጥለው ለአውሬ መፈንጫሆኗል።

7.ፋሽስቱ መንግሥቱ ሃ/ማ በጣም ያስጨንቀው የነበረው የኢሕአፓን እንቅስቃሴ እንጂ ወያኔዎችን አልነበረም ። የሠራዊቱን ትኩረት ሁሌ ኢሕአፓ ላይ እንዲሆን ትእዛዝ ይሰጥ ነበር እንጂ ወያኔዎችን ምቱ/አጥቁ የሚል እንዳልነበረ ከሞት ከተረፉት የደርግ ወታደሮች ተነግሯል ።ፋሽስቱ መንግሥቱ ወያኔዎችን በካድሬነት በመቅጠር ጭምር ነው ኢሕአፓዎችና ሌሎች ዲሞክራት ዜጎችን ያስጨፈጨፈው ።

8.ፋሽስቱ መንግሥቱ፡- በወታደራዊ ማዕረግ፣በዘመናዊ ውትድርና እውቀት ፣በዘመናዊ ትምህርትና በዘመናዊ አስተሳሰብ ከእሱ የሚበልጥ ፤ ለሕዝብ የቆመ፣የነቃ፣የሚጠይቅ፣ጀግናና አርበኛ ዜጋ መኖርም ሆነ ማየት ጭራሽ አልፈለገም። እነዚህን ዓይነት ሃይሎች ለሥልጣኑ አስጊ መስለው ይታዩት ስለነበረ ፤በ 17 ቱ የስልጣኑ ዓመታት የተለያዩ የጸረ-አብዮትነት ተቀጽላዎች ስም እየሰጠ-በከላሽኮቭ፣በኡዚ፣በመትረየስ ወዘተርፈ መነጠራቸው።

9.አባቶቻችን፣አያቶቻችን፣ቅድመ-አያቶቻችን ድንበር ጥሶ ከሚመጡ ባዕዳን ሆነ ከውስጥ ከሚነሱ ወራሪ ባንዳዎችና ሽፍቶች የሚከላከሉበትና የሚመክቱበት፣ የኖሩበትን ዘመን ያመረታቸው የነፍስ-ወከፍ መሳርያዎች ነበራቸው ።ከቅድመ መንግሥቱ መሪዎችና መንግሥታት ባልተለመደ ሁኔታ ያሮጌ ዘመንም ሆኑ የዘመኑ የጦር መሳርያዎች በዜጎች እጅ መኖር ለሥልጣኑ አስፈሪ መስሎ ስለታየው ፣ በተደጋጋሚ ወደ እያንዳዱ ዜጋ ቤት ትጥቅ አስፈቺ ቡድን በመላክ የጦር መሳርያ አልባ አደረጋቸው ።

10.ፋሽስቱ መንግሥቱ በዘረጋው ፀረ-ሕዝብ ሥርዓት፡-የዜጎዎችን አንደበት አዘጋ/አሳሸገ፣ቅስም ሰበረ፣ ስነ-ልቦና ገደለ፣አእምሮ አሸበረ፣አሸማቀቀ - ዳቦ፣ስኳር፣ዘይት፣ሹሮ፣ቡና፣ዱቄት ወዘተርፈ ጠፋ ወይም ተወደደ ብሎ መናገር ፀረ-አብዮተኛ አሰኘ፣አስረሸነ።ዜጎች መሄጃና መደበቂያ አጡ፤መፈጠራቸውን ረገሙ ፣የመንግሥቱ ከሥልጣ መወገት ተመኙ፣በዝምታ ፀለዩ።

በእነዚህና በሌሎች እዚህ ጋ ባልተጠቀሱ -ወደፊት ጥናትና ምርምር በሚ ያስፈልጋችው በርካታ ምክንያቶች መንግሥቱ ወያኔዎችን አጠናከረ፣ የወያኔዎች ቅስም/ሞራልና ስነልቦና አገዘፈ፣ዓላማቸውና ምኞታቸውን አሰመረላቸው/እውን አደረገላቸው። በመሆኑም ኢትዮጵያና የኢትዮጵያ ሕዝብ ለወያኔዎች ኢጋልጦና አመቻችቶ ወደ ዚምባቦይ ፈረጠጠ ።ፋሽስቱ መንግሥቱ እንደ እነዚህ ዓይነት ደባዎች ባይፈጽም ኖሮ-ወያኖች እንኳንስ ሊወሩንና ሊገዙን ከትግራይ ክልል አይወጡም ነበር ።ጀግናው የኢትዮጵያ ሠራዊትና ጀግናው የኢትዮጵያ ሕዝብ ለውርደት ያበቃው መንግሥቱ ነው።

ካልተሳሳትኩ ከ **6** ሳምንታት ፊት አንድ የፌስቡክ ሚዲያ አገልግሎት የሚጠቀም ጓደኛዬ ፣ ጠቅላይ ምኒስተር አቢይ 'መንግሥቱ ሃ/ማ የራሱን ውደቀት ያፋጠነው እሱ ራስ እንጂ በወያኔዎች ተሸንፎ አይደለም' ብለዋል ብሎ ነገረኝ ። እርሳቸው ከ **8** ሳምንታት ወዲህ እና ከ **6** ሳምንታት በፊት በነበረው የግዜ ገደብ ውስጥ ይናገሩት እንጂ፤ እኔ ፋሽስቱ መንግስቱ ሥልጣኑን ከተነጠቀበት ማግሥት ጀምሬ ስለውና ስከራከርበት የነበረና ያለ ነጥብ ነው ። በውስጠ ወይራም ቢሆን ለመንግሥቱ ሽንፈት ከላይ ባስ ቀመጥኳቸው ፕላስ**(+)** ምክንያቶች ነው ማለታቸው ይመስለኛል።

ስለሆነም እግዜር/አላህ እድሜዎን ያሰንብት**!** ያርዝም **!** አሚን**!**

ፋሽቱ መንግሥቱ ሃ/ማ ራሱና ቤተሰቡን ብቻ ይዞ አይደልም ወደ ዚንቧቤ የኮበለለው። ነዋይ/ገንዘብ እና ብሄራዊ ቅርሳ ቅርሶቻችን ይዞ ነው የፈረጠጠው ።

"… if Dr Abiy is to succeed in prosecuting criminal behavior by the former TPLF offi-cials, he cannot avoid addressing the still-outstanding criminal activities — including genocide — by the former *Dergue* officials who have been hiding in exile. Principal among these is Mengistu Haile Mariam, who led the *Dergue's* coup and ran the country from 1974 until 1991, when he fled into exile with very substantial stolen funds and as-sets belonging both to the nation and to Emperor Haile Selassie" **Gregory R. Copley, Editor :The Red Sea Emerging as a Key Global Strategic Dynamic Thanks to a Revolution Begun in Ethiopia:GIS/Defense&Foreign Affairs,Volum XXXVL,NO 43,August 3/2018,p6**

በግርድፉ ፡-ዶክተር አብይ የቀድም የትግሬ ሕዝብ ነጻ አውጪ ግንባር ባለስልጣኖች/ሃላፊዮች ቀድሞ ለፈጸሙትና አሁንም ለሚፈጽሙት ግልጽ ወንጀሎች በህግ እንዲጠየቁ ካደረጉ ፣ተደብቀው በስደት የሚኖሩት -የሰው ዘር በማጥፋት ወይም የገፍ ግድያ በመፈጸ ጭምር የሚፈለጉት ፣የቀድሞ የደርግ ባለስልጣኖችም ለፈጸሙት ወንጀል ለፍርድ ማቅረብ ይኖርባቸዋል/ለፍርድ የማቅረብ ግዴታ አለባቸው። ከእነዚህም ዋንኛው የሃይለሥላሴን መንግሥት የፈነቀለው ደርግ የመራውና አገሪቱ ከ 1974-1991 ዓ.ም የገዛው መንግሥቱ ሃ/ማር ያም ነው።መንግ ሥቱ በርከት ያለ ገንዘብና ንብረትነታቸው የአጼ ሃ/ሥላሴ የነበሩ ብሄራዊ ቅርሳ ቅርሶች ይዞ ኮብልዋል ይላል። ነገር ግንየመንግሥቱ ጀሌዎች ታማኝ ነው ፣ምንም ገንዘብ ይዞ አልሄደም ወዘተርፈ እያሉ ሲያወሩለት ይደመጥ ነበር።

በዲያስፖራው ዓልም የሚገኙ አንዳንድ ጋዜጠኛ ተብዮች -መንግሥቱ የኢትዮጵያ ባለውለታ ፣መታወስ የሚገባው ፣መደመጥ የሚገባው ፣አዋቂና ሕዝባዊ መሪ እንደነበረ አድርገው ወስብስብ የኢትዮጵያን የፖለቲካ ትኩሳት እንዲመክር ለቃለ መጠይቅ ደጋግመው ሲጋብዙትና ንግግሩን ሲጠቅሱ ሳዳምጥ ፤እንዲሁ ከእሱ ጋር ፎቶግራፍ ለመንሳት የሚጓጉና የሚፈልጉ ኢትዮጵያውያ መኖራቸውንሳይ እገረማለሁ ፤ምንያህል ኅሊናቢስ መሆናቸውም እታዘባለሁ ።

ሃ/ማርያም ደሳለኝ የዝምቧቤ አገራዊ መርጫ ለመታዘብ ሂዶ ከምንግሥቱ ሃ/ማርያም ጋር ፎቶ ተነስቶ ስለነበር- የሁለቱንም ምስል በተለያዩ በርካታ ሚዲያዎች ተለጥፎ -የደርግ ሹሟምንቶችና ካድሬዎች ሳይጨመሩ- ለዲያስፖራውና ለኢትዮጵያ አውደ ሕዝብ የወቅቱ መሳለቂያ ሆኗል። ይህንን በተመለከተ(Gregory R.Copley)የሚከ ተለውን አስተያየ ሰጥቷል።

"One of the rare shock waves which was sent through the Ethiopian community since Dr Abiy took office has been the meeting which took place in Harare, Zimbabwe, on August 1, 2018, between immediate past Prime Minister of Ethiopia Hailemariam Dessalegn and Mengistu. Hailemariam was in Zimbabwe as an election observer, but his beaming photograph alongside Mengistu belied the fact that Mengistu had been tried in absentia in Ethiopia in 2007 — under the Government which Hailemariam subsequently led — and was sentenced to life in prison for genocide" (Gregory,2018,p6)

በግርድፉ፡- ዶክተር አብይ ጠቅላይ ምኒስተር ኮሆኑ ወዲህ የኢትዮጵያ ማኅበረሰብ ወይም ኢትዮጵያውያን ካስገረሙ ነገሮች አንዱ- ትንሽ ቀደም ብሎ የኢትዮጵያ ጠ/ምኒስተር የነበሩት አቶ ሃ/ማርያም ደሳለኝ የዚምቧቤ አገራዊ ምርጫ ለመታዘብ በሄዱበት በዚምቧቤ ዋና ከተማ ሃራሬ እ.ኤ.አ<August 1/2018> ከመንግሥቱ ሃ/ማርያም ጋር ፎቶ ስለመነሳታቸውን ነው። አቶ ሃ/ማርያም ደሳለኝ ያማረና ፀሐያማ መስሎ ከመንግሥቱ ጋር የተነሳው ፎቶ የውሸት ወዳጅነት ፎቶ ነው። ምክንያቱም ሃ/ማርያም ደሳለኝ እ.ኤ.አ በ 2007 መንግሥቱ ሃ/ማርያም ባልተገኘበት በዘር ማጥፋት ወይም በገፍ ግዲያ ወንጀል የዕድሜ ይፍታህ እስር የፈረደባቸ ውን መንግሥት ተረክቦ የመራ ነው ፤ ማለት በመንግሥቱ ላይ የዕድሜ ዘመን የፈረደበትን የመለሰ ዜናዊ ግዛት አካል የነበረና እሱ ሲሞት ግዛቱና አገዛዙን ተረክቦ ኢትዮጵያ የገዛ በመሆኑ ጠላት እንጂ ወዳጅ ሊሆኑ አይችሉም ማለቱ ነው ።

መንግሥቱ ሃ/ማርያም ፀረ-የኢትዮጵያ ሕዝብ ነበር፣ ነው።ፀረ-ሕዝብ ብምንም ተአምር አገር ወዳድ አይሆንም።አንድ ሰው ፀረ-ዜጋ ከሆነ ፀረ-አገረ ነው፤ስለሆነም ደርጎችም ሆኑ ካድሬዎቻቸው ፀረ-ሕዝብም ፀረ-አገርም ነበሩ ፣ናቸው።

በዚህ ጽሁፍ ማስረጃዎችን ነጥቤ እንዳስጨበጥኩ - ወያኔዎች መንግሥቱ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ያበረከታቸው በረከቶች ወይም ስጦታዎች ናቸው። በሌላ አነጋገር ወያኔዎች መንግሥቱ ባነጠፈላቸውን አዳራሽ ነው የጨፈሩት ።ደርግ ማለት መንግሥቱ ፤መንግሥቱ ማለት ደርግ ስለሆነ-የኤርትራም መገንጠል ፤የአሰብና የምጽዋ የባህር በሮቻችን መወሰድ እና ኢትዮጵያ በወያኔዎች እንድ ትወረር ያመቻቸው መንግሥቱ መራሹ ድርግ ነው ባይነኝ፤ ነውም።